# የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ህግ ስልጠና ለዳኞች የተዘጋጀ

ሀብታሙ እርቅይሁን
(habtieerk@gmail.com)

በዳንግላ ከተማ ጥቅምት 2010 ዓ.ም.

# ዓላማዎች

- ፍትሐዊነት
- ዕውነትን መፈለግ- በክልሉ አሁን ያለበት ደረጃ እንዴት ነው? የሰበር ችሎቱ በዚህ ረገድ የገጠመው ተግዳሮት?
- Case management
- ወጭ ቆጣቢነት
- etc
- ዓላማዎችን ለማሳካት መታለፍ ያለባቸው ሂደቶች አሉ። ሁሉንም ባይሆን በተግባር የሚያከራክሩ ነጥቦችን እና ድንጋጌዎችን እናያለን።

# የፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን

- ስልጣን፡
  - በጉዳዩ ዓይነት
  - በተከራካሪዎች አይነት፣
  - አድራሻ፣
  - በገንዘብ ግምት ሊወሰን ይችላል
- ለፌደራል ጉዳዮች በዋናነት አዋጅ ቁ. 25/88.
- Article 5 Civil Jurisdiction

Federal Courts shall have jurisdiction over the following Civil cases:

1) cases to which a Federal Government organ is a party;

2) suits between persons permanently residing in Different Regions;

# የቀጠለ....

3) cases regarding the liability of officials or employees of the Federal Government in connection with their official responsibilities or duties;

4) cases to which a foreign national is a party; ,

5) suits involving matters of nationality;

6) suits relating to business organizations registered or formed under the jurisdiction of Federal Government organs;

7) Suits regarding negotiable instruments;

# የቀጠለ....

8) Suits relating to patent, literary and artistic-ownership rights;

9) Suits regarding insurance policy;

10) Application for Habeas Corpus.

- የክልል ስልጣን፥ አዋጅ ቁ.223/2007
- ለወረዳ ፍርድ ቤት፥

- በገንዘብ ተመን ለሚንቀሳቀስ ንብረት 300,000፤ ለማይንቀሳቀስ 500,000
- ልጅነት ይታወቅልኝ
- Habeas Corpus

# የቀጠለ....

- Issues

1.የተለያዩ ክልል ነዋሪ- federal interest

-አዲስ አበባ ክልል ናትን? ነዋሪዎችስ?

-ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ክርክር ሲኖራቸው

(25/88 ተፈጻሚ ነውን? ቀድሞ የሚኖሩበትን trace ማድረግ? for stronger reason የሚለውን argument መጠቀም?) which one is a better argument? ለስልጣን ክርክር የቀድሞ አድራሻ ይጠቅማልን?

- ባልና ሚስት የተለያየ ክልል ቢኖሩና የፍቺ ክርክር ቢቀርብ ጉዳዩ የፌደራል ይሆናልን? የሰበር መ/ቁ. 119582 እና 128844 ውሳኔዎች የባልና ሚስት ክርክር ጋብቻው በተፈጸመበት ክልል በሚገኝ የወረዳ ፍርድ ቤት ስልጣን ነው ማለቱ ህጋዊነት አለውን?
- ጋብቻው የተፈጸመበት ቦታ ወይም ክልል የግዛት ስልጣን ይወስናል እንጂ የስረ ነገር ስልጣን ሊወስን ይገባልን?

# የቀጠለ....

- የክልል የቤተሰብ ህግ ስልጣንን በተመለከተ የፌደራል አዋጅ ቁ. 25/88 ን ተቃርኖ ሊወጣ ይችላልን? ህጉ ተቃርኖ ቢወጣ ተፈጻሚነቱ እንዴት ነው?
- ውጭ ሃገር የተጋቡ ሰዎችን ይመለከታልን?
- Practical complications- በተጋቡበት ክልል ሀብት ሳያፈሩ ሌላ ክልል ሄደው ንብረት ቢያፈሩ ተጋቢዎቹ ወደተጋቡበት ክልል ተመልሰው ሀብት ካላፈሩበት ክልል ላይ መከራከራቸው ምክኒያታዊ ነውን?
- የመዘዋወር ነጻነትንስ በተዘዋዋሪ መልኩ አይገድብምን?
- In fact ተለያይተው የተለያየ ክልል ሲኖሩ የቆዩ ቢሆንስ?
- Irregular union ግንኙነት ውጤትን የተመለከተ ክርክር ቢሆን ኖሮ የተለየ ውጤት ይኖረዋልን?

2.የቼክ ክርክር- ቼክ እንደ ተላላፊ ሰነድ እና ተራ ሰነድ ሲሆን?

3. Habeas Corpus- በ25/88 እና በ223/2007 ግጭት አለ ወይስ የለም?

- ፍትሃብሄራዊ ከሆነ ክልል የራሱን ስልጣን መወሰን አይችልምን?

# የቀጠለ….

- የፌደራል መንግስት ክልል ስልጣን የለውም ባለው ጉዳይ የክልል አዋጅ ያለው ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው?
- ወይስ በፌደራል መንግስት አካላት ሲፈጸም 25/88 እና በክልል አካላት ሲፈጸም 223/2007?

4. የስ/ስ/ህጉ አንቀጽ 15(2)(ረ) የመንግስት ሰራተኛ ዕምነት በማጉደል ለሚቀርብ ክስ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ነው

- Procl. 223/2007 አንቀጽ15(2)(ረ)ን አሻሽሎልን?
- 5ሺ ያጎደለ ሰራተኛ ወረዳ ወይስ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ የት ይቀርባል?

5. ንብረት ለህዝብ ጥቅም ተብሎ ሲነሳ በልዩ ህግ ጉዳዩ የሚታይበትን አካል ካላመለከተ ወይም ተgሙ ካልተggመ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክሱ የሚቀርበው በክሱ ገንዘብ መጠን ወይስ በስነ ስርዓት ህግ ቁ. 15(2)(ሠ) መሰረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ?

   - በልዩ ህግ ጉዳዩ የሚታይበት አካል በተggመት ሁኔታ ምንም ካሳ ያልተወሰነላቸው ሰዎች ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉን ?

# የቀጠለ....

6.በስ/ስ/ህጉ አንቀጽ 40፣41፣43 የሚገቡ ተከራካሪዎች ስልጣንን ይወስናሉን?

- በ 41 መሰረት ለመግባት ያመለከተው ሰው ሲያመለክት ነው ስልጣኑን የሚወስነው ወይስ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ መብት እንዳለው ከወሰነ በ=ላ?
- አንድ ሰው ተከራካሪ (party to a suit) ነው የሚባለው መቼ ነው? ተከራካሪ ያልሆነ ሰው ስልጣን ሊወስን ይችላልን?
- ከፍተኛ ፍርድ ቤት የ 700 ሺ ብር ካሳ ክርክር እያከራከረ እያለ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 43 መሰረት መድን ድርጅት ወደ ክርክሩ ቢገባና የኢንሹራንስ ሽፋኑ 40ሺ ብር ቢሆን ክርክሩ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ሊቀጥል ይችላልን?
- በአንድ ክርክር ውስጥ ክልላዊና የፌደራል ጉዳይ ተብለው የሚለዩ ዳኝነቶች አሉን? የ40ሺ ብሩ የፌደራል ጉዳይ እና ቀሪው 660ሺ ብር ክልላዊ ጉዳይ?

# የቀጠለ....

- በዚህ ዓይነት ጉዳይ ከሳሹ በፍርድ ቤቱ ስልጣን ስር እንዲወድቅለት ክሱን በከፊል ቢተው ወይም ክሱን ላሻሽል ቢል ?

7. የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሲቀርብ አንቀጽ 17(3) ስልጣኑ በከፍተኛው ግምት ይወሰናል.

በተለይ ጉዳዩ በህግ ተለይቶ ሲሰጥ፡ ለምሳሌ መሬት የወረዳ ፍርድ ቤት ስልጣን ነው ; ተከሳሽ ሰብል ወይም ሌላ ንብረት ግምቱ ከወረዳ ፍርድ ቤት ስልጣን በላይ ክስ ቢያቀርብ ውጤቱ ምን ይሆናል? የመሬቱ ጉዳይ አብሮ ይተላለፋልን?ቢተላለፍ የሰበር ውሳኔን ይጥሳልን?

# የቀጠለ....

8. የስ/ስ/ህ/ቁ. 16(1) የክሱ አርዕሥት ክሱ የቀረበበት የገንዘብ ልክ or the value of the subject matter of the suit( English version) ?

- ዳኝነት በዝርዝር ተጠይቆ ድምሩ ላይ ግን የተወሰኑት ዳኝነቶች የገንዘብ መጠኑ ባይካተት የፍርድ ቤቱ ስልጣን እንዴት ይወሰናል?

9. የስ/ስ/ህ/ቁ. 358 መሰረት  የሚገባ ተከራካሪ ስልጣንን ይወስናልን?

- Retrial ሲወስን ወይስ rejection ስልጣን ይወስናልን?
- Rejection ለይግባኝ ምክንያት ይሆናል፡፡ ስለዚህ በይግባኝ ደረጃ ጉዳዩ የፌደራል ወይሥ ክልላዊ? ጉዳዩ በፍ/ስ/ስ/ህ.ቁ. 41 ለመግባት አመልክቶ አትገባም ከተባለ ተከራካሪ ይለያልን?

# የቀጠለ....

10. የክልል ሰበር ስልጣን- የፌደራል ጉዳይን የማየት ስልጣን የላቸውም

ነገር ግን የስር ፍርድ ቤት የፌደራልን ጉዳይ ያለስልጣኑ ካየ የክልል ሰበር ችሎት ጉዳዩን ለማረም የማየት ስልጣን አለው።

11. የከተማ ነክ እና የመደበኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ቀላቅሎ የያዘ ክስ የት ይቀርባል?

- Splitting of claims ጋር ያለው ቁርኝት እንዴት ይታያል?

# የቀጠለ....

12. የመንግስት ሠራተኞች የስራ ክርክር - የከተማ አስተዳደር ሠራተኞች ቀድሞ በደንብ ቁ.25/97 መሰረት በይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ታይቶ ይግባኙ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርባል

- ሌሎች ሠራተኞች አዋጅ 171/2002 መሰረት በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ታይቶ ይግባኙ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይቀርባል
- ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ከፈረሰ በ=ላ ጉዳዩ የት ይታያል?(አዲስ አዋጅ ይዘቱ ሌላ ካልሆነ በስተቀር)

# የክስ ምክንያት እና የመክሰስ መብት

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.231(1)(ሀ) መሰረት የክስ ምክንያት ክሱ እንደቀረበ ይመረመራል
  - ግን የክስ ምክንያት ምንድን ነው? Is it all about justiciable matters?
  - በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ክስ ማቅረብ ይቻላል ወይስ ቀጥታ የሰበር አቤቱታ ነው የሚቀርበው?
  - በህግ በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ በተፈቀዱበት ጉዳዮች ክርክሩ እንዴት ይመራል?
  - በተጠሪነት የሚጠራው ጉዳዩን የወሰነው መስሪያ ቤት ወይስ በውሳኔው የተጠቀመው ሰው?

# የቀጠለ....

- በመሬት አስተዳደር ውሳኔዎች ላይ ክርክሩ በግለሰቦች መካከል ሲሆን ጉዳዩ ከአስተዳደራዊ ወደ ፍትሐቤሄራዊ  የባለይዞታነት መብት ክርክር አይቀየርምን? ከተቀየረ ክርክሩ ህጋዊ ይሆናልን? እንደ ጣልቃ ገብ ሆኖ ቢገባ የክርክሩንይዘት ሳይቀየር መወሰን አይቻልምን ?
- ሰነድ አልባ ቤቶች ላይ ክርክር ቢቀርብ ፍርድ ቤቶች ሊወስኑ ይችላሉን ? ጉዳዩ የክስ ምክንያት አለውን ?
- የክስ ምክንያት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(2)(3) ከተመለከተው የመክሰስ መብት በምን ይለያል?
- የመክሰስ መብት መቼ ነው የሚመረመረው? ልክ እንደ ክስ ምክንያት ክሱ እንደቀረበ? ከ first hearing በ=ላ?

የክስ ምክንያት - ዳኝነት ሊጠየቅበት የማይገባ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ ካሳ፣ንብረት፣ውል የክስ ምክንያት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

# የቀጠለ....

- Defective የሆኑ ክሶች- ለምሳሌ ልጄ ቤት ስለሸጠች የሸያጩን ገንዘብ ታካፍለኝ የሚል ክስ( የቀድሞ ምዕራብ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበ ክስ ነው) - ከመነሻውም የክሱ ዝርዝር የከሳሽን መብት የማያሳዩ ከሆነ ተከሳሽ ክርክር አቅርቦ vested interest የለውም (Art. 33(2)) በማለት እንዲክድ መጠበቅ የስነ ስርዓት ህጉን ዓላማ ያሳካልን? ወይስ የክስ ምክንያት የለውም (Art. 231(1)(ሀ)) ሊባል ይገባል?
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33 vested interest
- 33(1)- ክስ ለማቅረብ ችሎታ ያለው- minority, interdiction- እንደታወቀ የሚመረመር
- 33(2)- በክሱ ነገር ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው
- 33(3)- በተከሳሽ ላይ የሚጠይቀውን ጥቅም እና መብት በማረጋገጥ
- Art. 33(2)(3) ተከሳሽ መልስ ከሰጠ እና ከካደ በኃላ ሊመረመር ይገባዋል- ወራሽ ያልሆነ ሰው ክስ አቅርቦ ተከሳሹ ቢያምንለት ምን ሊወሰን ይችላል?

# የቀጠለ….

- ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተግባር ላይ ለገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ካላቀረቡ፣ ለከተማ ቤት ካርታ ካልቀረበ የመክሰስ መብት የላቸውም የሚል ውሳኔ ይሰጣል፤ ተገቢ ነውን?
- በሌላ ማስረጃ የማስረዳት መብትን አይጋፋም?
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33 እና 231(1)(ሀ) ቀላቅሎ በመጥቀስ መወሰን የራሱ ችግር አለው። ሁለቱ conceptually ተመሳሳይ ናቸውን?
- የስረ ነገር ስልጣን እና የክስ ምክንያት res judicata effect የላቸውም
- የመውረስ መብት የለውም የተባለ ከሳሽ ግን ሁለተኛ ሊከስበት አይችልም
- ስለዚህ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(2)(3) እና 231(1)(ሀ) መካከል የሂደት እና የውጤት ልዩነት አለ ማለት ነው።

# መጥሪያ አደራረስ

1. መጥሪያ ከደረሰ የደረሰኝ መቅረብ አለበት

   በተግባር Art. 104 የተመለከተው የምስክር ዝርዝር አይፈጸምም

2. መጥሪያ ለመቀበል እምቢተኛ ከሆነ ወይም ደረሰኝ ለመስጠት እምቢተኛ ከሆነ በቃለ መሃላ ማመልከቻ ሲረጋገጥ መብቱ ይታለፋል

3. ተፈልጎ ከጠፋ እና በቃለ መሃላ ማመልከቻ ሲረጋገጥ ምትክ መጥሪያ- which means is better way of serving?

4. በባልና ሚስት ክርክር ተከሳሽ ባይቀርብ ፍቺ ሊወሰን ይችላልን ?

5. ከሳሽ መጥሪያውን ወጭ አድርጎ ወስዶ ወይም ሳይወስድ ለመልስ በተቀጠረበት ቀን ከሳሽም ተከሳሽም ቢቀሩ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 70(መ) ተፈጻሚነት አለውን ?

- ተጠርቶ ያልቀረበ መልስ የማቅረብ መብቱ ይታለፋል።

# መልስ የማቅረብ መብት መታለፍ ያለው ህጋዊ ውጤት

1. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.73(first hearing)፣72 እና during second hearing

- First hearing ላይ ከቀረበ ክርክር የማቅረብ መብት አለው
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.72

-ከ First hearing እስከ ቀጣዩ ቀጠሮ ከቀረበ

-በቂ ምክንያት ያለው

- የመከላከያውን ክርክር ማቅረብ ይችላል

Is it inclusive of the statement of defense?

# የቀጠለ....

- If one is appeared during second hearing, there are two arguments

  - first- በሌለበት ተብሎ የተሰጠውን ትዕዛዝ ካላስነሳ በክርክሩ ሂደት ሊሳተፍ አይገባም

  - second- በሂደቱ ሊሳተፍ ይገባል ማቅረብ የማይችለው የራሱን ክርክር እና ማስረጃ ነው:: So, cross-examination is possible.

- ግልጽ ድንጋጌ ከሌለ ዓላማውን የሚያሳካውን መከተል ተገቢ ነው::

# የቀጠለ....

2. የሚቀርበው ክርክር ወሰን (scope)

- መልስ የማቅረብ መብቱ የታለፈበት ተከራካሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማቅረብ ይችላልን?

- Art. 244(3) ቶሎ ተጠቃለው መቅረብ አለባቸው (ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት መሰናክል ከሚሆኑት በስተቀር - eg. የስረ ነገር ስልጣን)

- መልስ ያቀረበ ሰው በጽሁፍ ያላቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በ first hearing ጊዜ ማቅረብ ይችላልን?

- ልሎች ክርክሮችን በተመለከተስ?

# የቀጠለ....

3. ማስረጃ የማቅረብ መብት

- በ first hearing ጊዜ ማስረጃ መዘርዘር ለምሳሌ ምስክር ይቻላልን ?

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 137- ሰነድ ማቅረብ ይቻላልን?

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 256- መልስ ላላቀረበ ነገር ግን በሂደቱ እየተሳተፈ ያለ ተከራካሪ ተፈጻሚ ነውን?

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 249 እና 264 መሰረት ፍርድ ቤቱ መልስ የማቅረብ መብቱ የታለፈበትን ወይም በሌለበት የሚታይን ተከራካሪ ሊጠቅም የሚችል ማስረጃን ሊያስቀርቡ ይችላሉን?

- ማስረጃ ማቅረብ ካልተፈቀደ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 73 እና 72 መሰረት ክርክር እንዲያቀርብ መፍቀድ ምን ፋይዳ አለው?

# የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

1. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244(2) ላይ የተዘረዘሩት የክስ መቃወሚያዎች exhaustive ናቸውን? በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.216 የተመለከተው ክስን ነጣጥሎ ማቅረብ የክስ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም ማለት ነው?

- በእርቅ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረ ሀብት ቢገኝና ክስ ቢቀርብ ተነጣጥሎ የቀረበ ያስብለዋልን ?

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.216 እና 218(ሀ) መሬት ከአላባው ጋር አጣምሮ አለማቅረብ ክሱን ውድቅ ያስደርጋልን? የሰበር ውሳኔ
- የመሬት ክሱ ቀርቦ ከተወሰነ በኋላ ለሚገኝ ዓላባ ክስ ቢቀርብ የተነጠለ ያስብለዋልን?

# የቀጠለ....

- በባልና ሚስት ክርክር በሚንቀሳቀስ ንብረት ተከራክረው ካለቀ በ=ላ አዲስ ክስ በማይንቀሳቀስ ንብረት ቢቀርብ ክሱ ተነጣጥሎ የቀረበ ነው ያስብለዋልን ?
- ሚስት ከክርክር በ=ላ የተደበቀ የጋራ ንብረት ብታገኝና ክስ ብታቀርብ ክሱ ተነጥሎ የቀረበና ተቀባይነት የሌለው ነው ይስብለዋል?
- ፍርድ ቤት ዳኝነት ሳይጠየቅበት የተነጠለውን ሀብት ወይም ገንዘብ ክስ እንዲቀርብበት መብት ቢጠብቅ ውጤቱ ምንድን ነው? ፍርድ ቤት በህግ ያልተሰጠን መብት መፍጠር ይችላል ፍርዱ ካልተሻረ ውጤቱ ምንድን ነው?
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 216 ክስን ነጣጥሎ ማቅረብ ክርክሩ በፍርድ ቤት ሊነሳ ይችላልን? ስነ ስርዓት ህጉን የመምራት ግዴታ የፍርድ ቤቱ አይደለምን?

# የቀጠለ....

2. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 5 በፍርድ ያለቀ

- ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት- የስረ ነገር ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ ማለት ነው? Void judgment? የኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በአንድ ውሳኔ ዋና ጭብጥ ሳያደርግ የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው በተሰጠ ፍርድ ሊፈጸም አይገባም - የሰበር ውሳኔ የትኛው ክፍል ነው የሚያስገድደው ?
- Or ፍርድ ለመስጠት ስልጣን ባለው አካል{ courts and quasi-judicial organs} የተሰጠ ፍርድ ማለት ነው?
- አስተዳደራዊ ውሳኔዎች res judicata effect አላቸውን?
- የመጨረሻ ፍርድ- በስረ ነገር ስልጣን፣ በክስ ምክንያት አለመኖር የተወሰኑ?

# የቀጠለ....

- የክርክሩ ዓይነት እና ጭብጥ ተመሳሳይነት- ሁከት እና ባለቤትነት፣ በገጠር መሬት ባለይዞታዎች ከተከራከሩ በ=ላ መንግስት በቀደመው ክርክር የረታው አርሶአደር ላይ የባለቤትነት ክስ ቢያቀርብ?
- የተከራካሪዎች ተመሳሳይነት ወይም ከእነርሱ መብት ካገኙ ሰዎች- ከተጋቢዎች አንዱ በጋራ ንብረት ክስ አቅርቦ ቢረታ ሌላኛው ተጋቢ አዲስ ማቅረብ ይችላል? ሌላኛው ተጋቢ ሳያውቅ ቢሆንስ?
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 5(4)- ብዙ ሰዎች የሚያቀርቡት ሆኖ ከረቱ በክርክሩ ላልተካፈሉት res judicate effect አለው ከተረቱ ግን res judicata effect  የለውም

# የቀጠለ....

- በፍርድ ያለቀ የሚለው መቃወሚያ በፍርድ ቤት ሊነሳ  ይችላልን
- በአንድ ጉዳይ ሁለት የጸና ፍርድ ቢኖር የትኛው ሊፈጸም ይችላል

3. መቃወሚያዎች ላይ ክርክር ስለማድረግ

. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.245(1) -  መቃወሚያ ሲቀርብ ሌላኛው ተከራካሪ ክርክሩን እንዲያቀርብ መፍቀድ

- ማስረጃ መስማት

- ይርጋ ከተነሳ ይርጋው የሚgረጥበትን ምክንያት እንዲያቀርብ እድል ሊሰጠው ይገባል ማስረጃም መስማት ካስፈለገም መስማት ይገባል:: የማስረጃው ዓይነት የግድ አስቀድሞ የተዘረዘረ መሆን አለበትን?

# የቀጠለ....

- በመቃወሚያው ላይ ክርክር ለማድረግ በተቀጠረበት ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ባይቀርቡ ውጤቱ ምንድነው?
- በመቃወሚያ ላይ ክርክር እንዲያቀርብ ካልተፈቀደለት ያለው እድል በይግባኝ ጊዜ ማቅረብ ነው:: የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 329(1) ደግሞ አዲስ ክርክር ማቅረብን ይከለክላል:: ግን አዲስ ክርክር ተብሎ ውድቅ መደረግ አለበት ?
- ብዙ መቃወሚያዎች ኖረው በአንዱ ብቻ ከተወሰነና ጉዳዩ በይግባኝ ከተሻረ ሌሎች መቃወሚያዎችን መመርመር ይገባል።

# የፍሬ ነገር ክርክርን መስማት

- የመደመጥ መብት የሚረጋገጥበት ነው
- ክርክርን ለመምራት፣ የክርክራቸውን ልዩነት ለመመልከት እና ጭብጥ ለመመስረት አስፈላጊ ሂደት ነው

- የጭብጥ ዓላማ- ፍትህ እንዳይዛባ በማድረግ ክርክሩን ለመምራት
  - የማስረዳት ሸክሙ የማነው የሚለውን ለመለየት
  - ጊዜና ወጭን ለመቆጠብ
  - ጥሩ የፍርድ አጻጻፍ እንዲኖርም ያደርጋል

-

# የቀጠለ....

- በተግባር ዳኞች ዝግጅት ሳናደርግ ክስና መልሱን ሳናነብ ተከራካሪዎችን ምን ትላላቹህ በማለት ክርክሩን ስለምንመራ ዓላማዎቹ ሳይሳኩ ይቀራሉ
- አንዳንዴ በሌላ ቀጠሮ የማጣራት ስራ በመዝገቦች ላይ ተሰርቶ ይገኛል
- አንዳንዴ አዲስ ዳኝነት ተጠይቆበት ይገኛል፡፡ ከተጠየቀው ዳኝነት በከፊል በክስ መስማት ጊዜ መተው ይቻላልን?
- በክስ መስማት ጊዜ የተከራካሪዎች አለመቅረብ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 69 እና 73 የተመለከቱትን ለመፈጸም ያስችላል ነገር ግን during second hearing በምስክር መስማት ወይም ማስረጃ መቀበል ጊዜ እነዚህ ድንጋጌዎች ይፈጸማሉን?

# የማስረጃ አቀባበልና መስማት ሂደት

- ማስረጃ ምንድን ነው-
- ፍሬ ነገርን ወይም በጭብጥነት የተያዘን ጉዳይ መኖር አለመኖርን ለማሳየትና ለማሳመን የሚቀርብ ነው
- አለ ወይም የለም የተባለውን ነገር ዕውነተኛነት ወይም ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ ነው
- ስለዚህ የሚከተሉት  ነገሮች ማስረጃ አያስፈልጋቸውም ማለት ነው

1. ህግን የሚመለከት ክርክር- ነገር ግን የህግ ክርክርን ከመወሰናችን በፊት ማስረጃ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ የስረ ነገር ስልጣን ለመወሰን የት ክልል እንደሚኖር ማረጋገጥ ያስፈልጋል

# የቀጠለ....

2. የታመነ ነገር ማስረጃ አያስፈልገውም:: ግን በምን ሁኔታ የት የታመነ?- መልስ ሲያቀርብ አምኖ በቃል ክርክር ቢክድ?

- በሌላ ፍርድ ቤት በሌላ ጉዳይ አንድ ፍሬ ነገር ቢያምን አሁን በተያዘው ጉዳይ ያለው ውጤት ምንድን ነው?

- የታመነውን ፍሬ ነገር መልስ ወይም ክስ ሲሻሻል ተክዶ ቢቀርብ ህጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው?

- የታመነ ፍሬ ነገርን ጉዳዩ በስልጣን ምክንያት ሲዘጋ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተክዶ ቢቀርብ?

# የቀጠለ....

- በመሸሸ የተሰጠ መልስ እንደተካደ ይቆጠራል ለካሳ ጥያቄ የቀረበውን የገንዘብ ልክ በስተቀር ( የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 83 ) ካሳ ምንድን ነው? በፍ/ህ/ቁ. 2118 መሰረት ዕቃዎቹን ማስመለስ ካሳ ነው። ስለዚህ ካሳ ከንብረት ክርክር በምን ይለያል? በካሳ ክርክር ምኑ ነው የሚካደው?

- መልስ አቅርቦ በግልጽ ያልካደውን እንደታመነ ከተቆጠረ መልስ የማቅረብ መብቱ የታለፈን ወይም በሌለበት የሚታይን ተከራካሪ እንደካደ መቁጠር ምክንያታዊነት ነው ወይ?

# የቀጠለ....

3. ፍርድ ቤት ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ነገሮች- እንደ ህዝብ በዓላት ቀናት
4. የህግ ግምት - ከአንድ ከተረጋጋጠ ፍሬ ነገር በመነሳት ሌላ ፍሬ ነገር ትክክለኛነት መገመት ማለት ነው- ለምሳሌ በፍ/ህ/ቁ. 2020 መሰረት ዋናውን የዕዳ ሰነድ መመለስ ዕዳው እንደተከፈለ ያስቆጥራል

- ማስረጃ የሚቀርቡበት መንገዶች

1. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 223 እና 145- ከክስና መልስ ጋር የሚቀርቡ ናቸው። የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 145 የማስረጃው ዝርዝር ቀርቦ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የሚቀርቡ ናቸው ማስረጃ የሌለው ክስ እና መልስ ሊቀርብ ይችላልን? ዐ/ህግ ተወክሎ ለሚከራከርላቸው ተ9ማት ከዛው ለሚገኙ ማስረጃዎች የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 145ን ይጠቀማሉ ተገቢ ነው ትላላቹህ?

# የቀጠለ....

2. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.137 ማስረጃ የሚቀርበው- ከመጀመሪያው ቀጠሮ በፊት or first hearing በፊት የሰነድ ማስረጃን የሚመለከት ነው

A. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.223 ተዘርዝሮ ያልቀረበ?

B. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.145 ተጠይቆ ያልቀረበ?

C. አስቀድሞ ያልቀረበበትን ምክንያት በበቂ ሁኔታ ለሚያስረዱ?

D. ማናቸውም ዓይነት የሰነድ ማስረጃ በቂ ምክንያት ሳይጠየቅ ?

- መልስ ያላቀረበ ተከራካሪ ያለው መብት? ክርክር ሳያቀርብ ምን ሊያስረዳ ማስረጃ ሊያቀርብ ይችላል ?

# የቀጠለ....

3. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.256 - በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 137 እና 249 መሰረት መቅረብ የሚገባቸው ማስረጃዎች ሳይቀርቡ ለቀሩት ማስረጃዎች- ይህ ማለት በዚህ ድንጋጌ መሰረት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ክሱ ከተሰማ በኋላ ፍርድ እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ነው ማለት ነው?

- በቂ ምክንያት ሲቀርብ
- ነገሩ የሚሰማበትን ቀጠሮ

ይወስናል

- ብዙ ጊዜ አዲስ የተገኘ ማስረጃ የሚቀርብበት ነው

# የቀጠለ....

- መልስ ያላቀረበ ተከራካሪ ክሱ ሲሰማ ቀርቦ ከተከራከረ እና አዲስ ማስረጃ ካገኘ ማቅረብ ይችላልን

4. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 264 ፍርድ ቤቱ በራሱ ስልጣን የሚያስቀርባቸው ማጣሪያ ማስረጃዎች

5. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 40 መሰረት ተከሳሽ ሲጨመር ወይም ክስና መልስ ሲሻሻል?

# የቀጠለ....

- ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ የሚስቀርባቸው ማስረጃዎች፡

  - በተግባር ስልጣኑን ያለመጠቀም- ክርክሩ እንደገና እንዲታይ ምክንያት ይሆናል

  - ማስረጃዎች ከቀረቡ በ=ላ ለተከራካሪ ያለማሳወቅ፣ ሚስጥራዊ ማድረግ፣ በተከራካሪዎች ሲጠየቅም የፍርድ ቤቱ ማስረጃ ነው ብሎ ማለፍ፣ ይዘቱ እንèን ክርክር እንዲያቀርቡበት ዕድል ያለመስጠት ይታያል።

  ነገር ግን ፍርድ ቤቱ የያዘው የተከራካሪዎች ጉዳይ ነው። due process right ማክበር ማለት ማስረጃው ላይም ተከራካሪዎች ዕድል እንዲኖራቸው ማድረግም ያስፈልጋል ። ካልተደረገ

# የቀጠለ....

1. የፍ/ስ/ስ/ህጉ በክስና መልስ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ለተከራካሪ እንዲደርስ ማዘዙ፣ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 137 መሰረት ክስ ከመሰማቱ በፊት እንዲቀርብ መደንገጉ፣ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 256 የሚቀርቡ ማስረጃዎች ላይ በማስረጃው ላይ ክርክር ለማድረግ ቀጠሮ እንዲሰጥ መጠየቁ- የመደመጥ ዓላማን መያዙን በግልጽ መረዳት ይቻላል። ካልተፈጸመ ዓላማውን ይስታል

2. misperception , loss of public trust and confidence እንዲኖር ያደርጋል

# የቀጠለ....

3. በተግባር ችግር ያመጣል። የሚቀርቡት ማስረጃዎች ሁሉ ትክክልና ተገቢ ስለማይሆኑ - ለምሳሌ- የመሬት አስተዳደር ማስረጃዎች ችግሮች ያሉባቸው ይኖራሉ- ችግሩን ለመቀነስ ለማስረጃው አሰባሰብ ቅርብ የሆኑትን ተከራካሪዎች እንዲሰሙ ማድረግ ያስፈልጋል። In doing so we can achieve the search of truth objective of civil procedural law.

# የቀጠለ....

- የፍ/ስ/ስ/ህ.ቁ. 78፣ የእግድ ክርክሮች፣ የመጥሪያ አደራረስ ክርክሮች ማስረጃ አቀራረብ የፍ/ስ/ስ/ህ.ቁ.223 ን ይከተላልን
- በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢቀርብ ተከራካሪዎች  ማስረጃ እንዴት ያቀርባሉ ?
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.199 እና 256(1)- ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ማስረጃ ባይቀርብ ውጤቱ መዝገብ መዘጋት ነውን ወይስ በሌለበት ማለት ? ታልፎ ፍርድ ከተሰጠ ያላቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን መቼ ያስረዳል ?
- የምስክር አቀባበልን በተመለከተ

  - ጭብጥ ሳይዙ መጥራት- ከተያዘው ጭብጥ ውጭ እናሲያዝ ቢሉ?

# የቀጠለ....

- ምስክሩ በጉዳዩ ላይ ድምዳሜውን ገልጾ ድምዳሜው ላይ ለመድረስ የተጠቀመበትን መንገድ ሳይገልጽ መቅረት- ለምሳሌ- መሬቱ የከሳሽ ነው ካለ ምስክሩ መሬቱ እንዴት እንደተገኘ፣ የከሳሽ መሬት መሆኑን እንዴት እንዳወቀ መጠየቅ አለበት

( direct or indirect knowledge እንዳለው መጣራት አለበት)

- ምስክር መጠየቅ የማይችሉ ተከራካሪዎች ሲኖሩና ምስክርን በመጠየቅ የዳኞች ሚና ምን መሆን አለበት? ማጣሪያ ጥያቄ ማለት ምስክሩ ተናግሮ ግልጽ ላልሆነው ማለት ነው ወይስ ዕውነቱን ለማጣራት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መጠየቅ አለበት?

# ተከራካሪዎች ወደ ክርክሩ የሚገቡበት ስርዓት

1. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 40- ተከራካሪዎቸን መጨመርና መተካት

   - የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 40(2)-

   የፍርድ ቤቱ ስልጣን ነው፡፡ ይህን ስልጣን አለመጠቀም ጉዳዩ እንደገና እንዲመለስ ምክንያት ይሆናል

2. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41- ጣልቃ-ገብነት

   - ዳኝነት ክፍያ- በከሳሽነት ሲገባ - በመርህ ደረጃ ከሳሽ ዳኝነት መክፈል አለበት፡፡ ነገር ግን ከሳሽ ከከፈለው ድጋሜ ክፍያ መጠየቅ ተገቢ ነውን? ከሳሽ የከፈለውን ጣልቃ ገቢው እንዲጋራው መጠየቅ ይችላል፡፡

# የቀጠለ....

- በተከሳሽነት ለሚገቡ የዳኝነት ክፍያ አይመለከታቸውም፡፡
- በከሳሽነት የሚገቡት ዋናውን የክስ ዳኝነት መቀየር ይችላሉን? ከሳሽ የውርስ ቤት በድርሻው ቢጠይቅ ጣልቃ የገባው ሌላ ወራሽ ቀሪውን ድርሻ መጠየቅ ይችላልን?
- ጣልቃ ለመግባት መከተል ያለብን Procedure- ጣልቃ ለመግባት ማመልከቻ ማቅረብ፣ መብቱ ላይ መወሰን የፍርድ ቤቱ ስልጣን ነው ወደ ክርክሩ ከገባ ማመልከቻው ለተከራካሪዎች ይደርሳል በተለይ በከሳሽነት የሚገባ ከሆነ ተከራካሪዎች በጽሁፍ መልስ ሊያቀርቡበት ይገባል፡፡

# የቀጠለ....

- በተከሳሽነት የገባ ሰው ዋናው ተከሳሽ ያላነሳውን ክርክር ለምሳሌ- የይርጋ ክርክር ማንሳት ይችላልን? ከቻለ ውጤቱ ምንድን ነው? ዋናውን ተከሳሽንም ይጠቅመዋልን? በአንድ ዘንግ የሚቆሙ(debtors jointly and severally liable-civil code art. 1896 and the ff.) እና የማይቆሙ ተከሳሾች መካከል ልዩነት አለን?

- ጣልቃ ገብ የፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣንን የማስቀየር ሁኔታን ሊፈጥር ይችላልን?

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ጣልቃ ለመግባት አመልክቶ አይገባም የተባለ ሰው ይግባኝ ባያቀርብ, በተመሳሳይ ጉዳይ አዲስ ክስ የማቅረብ መብት አለውን?

# የቀጠለ....

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ጣልቃ ለመግባት አመልክቶ አይገባም የተባለ ሰው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 መሰረት ከፍርድ በ=ላ መቃወሚያ ማቅረብ ይችላልን?

ጣልቃ ለመግባት አመልክቶ አይገባም የተባለ ሰው እንደ ተከራካሪ ይቆጠራልን በሌላ በኩል በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 መሰረት መቃወሚያ ለማቅረብ የፌ/ሰ/ሰ/ችሎት ክርክሩን የማያውቅ ሰው መሆን አለበት ማለቱ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ህጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው ?

# የቀጠለ....

- በይግባኝ ደረጃ ባለ ክርክር በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ጣልቃ መግባት ይቻላልን? ከፍርድ በ=ላ pending case ላይ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 መሰረት መቃወሚያ ማቅረብ ይችላልን?
- ከ remand በ=ላ ጣልቃ መግባት ይቻላልን?
- ጣልቃ ገብ ከክርክሩ በ=ላ ክርክር ባልተደረገባቸው ንብረቶች አዲስ ክስ በተከሳሽ ላይ ቢያቀርብ ክሱ ተነጣጥሎ የቀረበ ያስብለዋልን?

3. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 43 የሶስተኛ ወገኖች ጣልቃ መግባት (Impleader, Joinder of third party)

- ወደ ክርክሩ ከሚገባው ወገን ጋር ተከሳሽ ያለውን ግንኙነት መግለጽ ነው ወይስ ማስረዳት ነው ያለበት ?

# የቀጠለ....

- ወደ ክርክሩ እንዲገባ መወሰን የፍርድ ቤቱ ስልጣን ሲሆን የከሳሽ ክስና መልስ ተልኮለት መልስ ያቀርባል ክርክሩ ይሰማል

- በካሳ ክርክር ተከሳሽ ያለነሳውን የይርጋ ክርክር መድን ድርጅቱ ቢያነሳው ውጤቱ ምን ይሆናል? ተከሳሹ ያመነውን ሃላፊነት መድን ድርጅቱ መካድ ይችላልን?

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.43 መሰረት የሚገባው ተከራካሪ ለተከሳሽ ሀላፊነት የለብኝም ቢል?

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.43 መሰረት ሲገባ ዋናው ተከሳሽ ከክርክሩ ይወጣልን?

# የፍ/ስ/ስ/ህግ ሌሎች ክርክሮች

1. ክስ እና መልስ ስለማሻሻል- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 91

- በተከራካሪዎች ጥያቄ ወይም በፍርድ ቤቱ አስተያየት ሊሻሻል ይችላል

- የተከራካሪዎች ጥያቄ በግልጽ ምክንያቱ ተጠቅሶ መቅረብ አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱም ሲያዝ የሚሻሻለውን በግልጽ ዘርዝሮ መሆን ይገባዋል ተሻሽሎ ሲቀርብም በትዕዛዙ መሰረት መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይገባል

- ተከሳሽ በሌለበት እየታየ ክሱ ቢሻሻል ለተከሳሽ መጥሪያ ሊላክ ይገባልን ?

# የቀጠለ....

- የታመነ ፍሬ ነገር ሲሻሻል ተከዶ እንዳይቀርብ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል

- የክሱን የገንዘብ መጠንስ መጨመር ይቻላል?

የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.91(5)- ክሱ ሲሻሻል ከፍርድ ቤቱ ስልጣን በላይ ካደረገው

- cause of action መለወጥ ይችላልን?

2. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 250- የግምት ተቃውሞ- የክሱን ሀብት መጠን መቃወምና የሀብቱን የዋጋ ግምት መቃወም ይለያያል

- ተገምቶ ሲመጣ የክሱ ሀብት መጠን ከፍርድ ቤቱ ስልጣን በታች ወይም በላይ ቢሆን የፍርድ ቤቱን ስልጣን ይቀይረዋልን ?

# የቀጠለ....

3. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 74- መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ውስጥ ካላመለከተ መዝገቡን ማንቀሳቀስ አይችልም። ነገር ግን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያላመለከተው በቂ እክል ገጥሞት ቢሆንስ? እክል ካለ እስከመቼ መጠበቅ አለበት ?

4.ዕግድ፣ማስከበርና ዋስትና

- ከፍርድ በፊት ንብረት ለማስከበር-የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 151-153-ንብረቱን ለማሸሽ ወይም ለማባከን ማቀዱ ከተረጋገጠ ተከሳሹ ዋስትና እንዲሰጥ ወይም ዕቃው ወይም ንብረቱን እንዲያቀርብና እንዲከበር የሚደረግበት መንገድ ነው

- ለጊዜው የሚሰጥ የማገድ ትዕዛዝ (injuction)-የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.154-ንብረቱ እንዳለ እንዲቆይ፣ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ፣ ወደ ሌላ ስፍራ እንዳይዛወር የሚታገድበት ነው።

# የቀጠለ....

- ከክሱ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ሃብት
- ንብረትን ማገድ judicial mortgage effect አለው

  የዕግድ ትዕዛዝ ክርክር ተደርጎበት ሊነሳ ወይም ሊሰረዝ የሚችል ነው (የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.158)
- የዕግድ ትዕዛዝ ወሳኔ ሲሰጥ ሊነሳ ይገባልን ? ከተነሳ የፍርድ ባለመብት ፍርዱን በምን ንብረት ሊያስፈጽም ነው ?
- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 200 እና ተከታዮቹ መሰረት የሚሰጥ ዋስትና- ተከሳሹ ሊደርስበት ስለሚችለው ኪሳራ ከሳሹ ዋስትና ወይም መያዣ እንዲሰጥ ወይም ዋስ እንዲጠራ የሚደረግበት

  ይህ ከሳሹን የሚመለከት ሲሆን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 151-153 እና 154 የተገለጹት ተከሳሽን የሚመለከቱ ናቸው

5. የተለያዩ አቤቱታዎች (የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 78፣256፣ ዕግድ የመሳሰሉት) በማመልከቻ ሲቀርቡ አንቀበልም ማለት ወይም ተቀብሎ ትዕዛዝ ያለመስጠት

# የቀጠለ....

6. ዕርቅ- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 277 እና 278

- ዕርቁን ከማጽደቅ በፊት የግራ ቀኙን ስምምነት በማንበብ ፈቃዳቸውን ማረጋገጥ ይገባል

- የዕርቁ ስምምነት በተከራካሪዎች ወይም ልዩ ውክልና በያዘ ሰው መፈጸም አለበት። ነገር ግን ዕርቁን ያለተከራካሪዎች በጠበቃ አማካኝነት ቀርቦ ሊጸድቅ አይችልምን ? ዕርቅ ማጽደቅ የክርክር ስርዓት አካል አይደለምን ? ጠበቃ ክርክር እንዳያቀርብ መከልከል አይሆንምን ?

- ዕርቁ በአንዱ ወገን ቢካድ ውጤቱ ምን ይሆናል በማስረጃ አረጋግጦ መፈጸሙ ከተረጋገጠ ማጽደቅ ወይስ እንደካደው ዕርቁን ውድቅ ማድረግ?

# የቀጠለ....

- ዕርቅ በፍርድ ቤቱ ዕውቅና የተደረገ እና ከዕውቅና ውጭ መደረጉ ለማጽደቅ የ procedure ልዩነት አለውን ?
- በባልና ሚስት ክርክር ስለፍቺ ውጤት ስምምነት ፈጽመው ቢቀርቡ የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 91(3) መሰረት ስምምነቱ የልጆችን ወይም የአንደኛውን ተጋቢ መብት ከጎዳ እንዲስተካከል ያዛል፡፡
- ሌሎች ስምምነቶችን ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ካልሆኑ በቀር ይዘታቸው ይስተካከል የማለት ስልጣን ፍርድ ቤት አለውን ?

# የቀጠለ....

- እርቅ ከጸደቀ ውጤቱ እንደፍርድ ስለሆነ ተገዶ ይፈጸማል ስለዚህ ዕርቅ መቀጮ ያስፈልገዋልን? መቀጮ ተካቶ ሲመጣ ከስምምነቱ እንዲወጣ መደረግ አለበት ወይስ መቀጮው አብሮ መጽደቅ አለበት? ከመዋዋል ነጻነት አንጻር እንዴት ይታያል?
- ዕርቁ ከነመቀጮው ከጸደቀ ፍርዱ እንዴት ይፈጸማል? መቀጮው በአፈጻጸም ችሎቱ ሊታይ ይችላልን? ውል አፍራሹ ማነው የሚለው ማስረጃ መስማትም የሚያስፈልገው ከመሆኑ አንጻር አፈጻጸም ችሎት ፍሬ ነገር አጣርቶ መወሰን ይችላልን? በማስረጃ ተጣርቶ የሚፈጸም ፍርድ አለን?

# የቀጠለ....

- ዕርቁ ላይ ተከራካሪ ያልሆነ ሰው ታርቆ ቢቀርብ ተካቶ እርቁ ሊጸድቅ ይገባልን? ቢጸድቅ የፍርድ ባለመብት መሆን ይችላል? ተከራካሪ ያልሆኑ ሰዎች የሚለው በባልና ሚስት ክርክር ስለ ልጆች አስተዳደግ ባልና ሚስቱ ተስማምተው የሚመጡትን አያካትትም።
- በዕርቅ ላይ ለመንግስት መቀጮ እንዲከፈል ቢስማሙና ዕርቁ ቢጸድቅ መንግስት የአፈጻጸም ክስ ሊያቀርብ ይችላልን ?
- ዕርቁ ላይ ክርክር ወይም ዳኝነት ያልተጠየቀበት ንብረት ተካቶ ቢገኝና ቢጸድቅ በአፈጻጸም ሊጠየቅ ይችላልን?

# በአጭር ሁኔታ የሚወሰኑ ክርከሮች

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 284 -የጉዳዩ ዓይነቶች- ውል፣ቼክ፣ባለእዳነት የሚገልጽ ውል፣ በሂሳብ በተጣራ ሰነድ ገንዘብ ለመክፈል በተደረገ ስምምነት፣ ዋስትና ውል የሚመለከት ሲሆን
- በመሃላ ቃል የተደገፈ
- የስ/ስ/ህጉ ሰንጠረዥ 2፣ ቁጥር 2-የመጥሪያው ፎርም- መጥሪያ በደረሰዎ በ 10 ቀናት ቀርበው ክሱን ለመከላከል ፈቃድ እንዲጠይቁ

# የቀጠለ....

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 285- በዚህ ስንጠረዥ ወይም ተስማሚ ነው ብሎ በሚገምተው ሌላ ፎርም የሚለው 10 ቀናቱን ፍርድ ቤቱ ማሳጠር ሆነ ማስረዘም ይችላል ማለት ነው?
- ዋሱ አብሮ ተከሶ ዋናው ባለዕዳ መከላከያ ሲያቀርብ ዋሱ ባያቀርብ ዋሱ ላይ አስቀድሞ የዋናው ባለዕዳ ሃላፊነት ሳይወሰን ፍርድ መስጠት ይቻላልን?
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 286(2) -በተከሳሽ ዕጅ ያለውን ሰነድ ይመረምራል። ሰነድ ያለው የጉዳዩ ዓይነቶች በሰነድ የሚረጋገጡ ስለሆነ ነው ነገር ግን ፈቃዱ ጉድለት ያለበት ነው ቢል በሰው ምስክር ሊረጋገጥ አይችልምን?

# የቀጠለ….

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 286(3)- የተከሳሽ መከራከሪያ ለከሳሽ ሊደርሰው ይገባል፡፡ ከሳሽ ክርክር ማቅረብ ስለመቻሉ የተገለጸ ነገር የለም ክርክር ያቅርብ ከተባለ ክርክሩ ማስረጃን የመጋበዝ ዕድል ስላለው ጉዳዩን ከዓላማው ውጭ አያÒትተውምን ?
- የተከሳሽ ክርክር ተቀባይነት ካገኘ ወደ መደበኛው የክርክር ዓይነት ይመለሳል
- የተከሳሽ ክርክር ተቀባይነት ካላገኘ ወዲያውኑ ፍርድ ይሰጣል፡፡

# ከፍርድ በኋላ ጉዳይ የሚታይበት ስርዓት

1. ዳግም ዳኝነት- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 6

   - በተሳሳተ ማስረጃ የተወሰነ ከሆነና የማስረጃው ይዘት መለወጡ ከተገለጸ ወይም የተሳሳተ ማስረጃ እንደሆነ ማስረጃውን የላከው አካል ድጋሜ ዳኝነት ለማየት በቂ ነው (የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቅጽ 15 ላይ ወሳኔ)

   - ባወቀ በአንድ ወር ጊዜ- ፍርድ ቤቱ ሊያነሳው የሚችል የስነ ስርዓት ህግ ይርጋ

   - በውሳኔው ላይ ይግባኝ ቢልም ባይልም

   - ዳግም ዳኝነት ሊታይ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጉዳይ ይግባኝ አይባልበትም ስለዚህ ሊታይ ይገባል በመባሉ ፍሬ ጉዳይ ሳያልቅ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት ይችላልን?

# የቀጠለ....

- በተግባር የአንድ ወር ይርጋው በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሲነሳ ይታያል፡፡ ተገቢ ነውን ?

2. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ፍርድ ላይ መቃወሚያ ስለማቅረብ

- ፍርዱ መብቱን የነካበት ሰው

- ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት

- ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት የሚቀርብ- ሰበር ችሎት ቢሆንስ?

- መብቴ ተነካ ያለው ሰው ከሌላ ክልል ነዋሪ ቢሆን ወይም የፌደራል መንግስት ተመዝጋቢ ድርጅት ቢሆን የፍርድ ቤቱን ስልጣን ይቀይረዋልን? ከቀየረው መዝገቡ ይተላለፋልን?

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 358 ከአዋጅ ቁ.25/88 አንጻር special ነውን

# የቀጠለ....

- ስልጣኑን የሚቀይረው ማመልከቻውን እንዳቀረበ ነው ወይስ ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ በ=ላ?

- ጉዳዩ በይግባኝ ክርክር ላይ እያለ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 358 መሰረት በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መቃወሚያ ማቅረብ ይቻላልን? መቃወሚያው ቀርቦ ሌላ ውሳኔ ቢሰጥና በተመሳሳይ ጉዳዩን የያዘው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የመጀመሪያውን ውሳኔ ቢያጸናው ውጤቱ ምን ይሆናል?

- የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 67127 ቅፅ 13 ላይ የሰጠው ውሳኔ አንድምታ ምንድን ነው ?

- በይግባኝ ፍርዱ ከተለወጠ መቃወሚያው የት ይቀርባል ?

- የጸደቀ ዕርቅ መብቱን የነካው ሰው ወይም ነጻ ፈቃዴን አልሰጠሁም ቢል- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 274(2) መሰረት የፍ/ህ/ቁ. 3307-3324 ተፈጻሚነት አለው ?

# የቀጠለ....

3. ይግባኝ

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 327(3) እና 345 በይግባኝ ደረጃ ማስረጃ የሚቀርብባቸው ድንጋጌዎች- በስር ፍርድ ቤት ያልተሰማ፣ ፍርድ ቤቱ የሚያስቀርበው

- በይግባኝ ደረጃ አዲስ ማስረጃ ቢገኝስ? የማስረጃው ይዘት ቢለወጥ ዳግም ዳኝነት ወይስ ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ይታያል? ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገሩን ትክክለኛነት የማጣራት ሀላፊነት የለበትምን?

- በይግባኝ ማስረጃ መስማት ወይስ እንዲሰማ ወደ ስር ፍርድ ቤት መመለስ ? (የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 346(ሀ) ራሱ በመቀበል ወይም የስር ፍርድ ቤት እንዲቀበል በማዘዝ) ማስረጃ በአዲስ መልክ ሲሰማ እና በስር ፍርድ ቤት የተሰማውን ማጣራት ልዩነት ሊኖረው አይገባምን ?

# የቀጠለ....

- ይግባኙ በቅሬታው መሰረት ይመረመራል። የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 182(2) እና 328(3)- ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በቅሬታው ከተዘረዘረው ውጭ አከራክሮ መወሰን ይችላል። scope የት ድረስ ነው? በውርስ ወይም በባልና ሚስት ክርክር ቤት ላይ ቅሬታ ቀርቦ በስር ፍርድ ቤት በተከራከሩበት ሌላ ንብረት ለምሳሌ መኪና ላይ መወሰን ይቻላልን? ወይስ ቤቱ ላይ  ቅሬታ አቅርበው ክርክሮችን exhaust አድርገው ባያቀርቡም በስር ፍርድ ቤት በአግባቡ ያልታዩ ነጥቦችን የመመርመር ስልጣን ነው?

# የቀጠለ....

- ያስቀርባል ሲባል በግልጽ ያልጸና ጉዳይ ሁሉ  እንደጸና ሊቆጠር አይገባም በፍርድ ጊዜ መወሰን አለበት። ያስቀርባል ባልተባለበት ነጥብ ይግባኝ ቢቀርብበትም ውሳኔ ያላገኘ ነው ተብሎ ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ነው። የአፈጻጸም ዕግድ ለመስጠትም አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን መልስ ሰጭው ክርክር ያላቀረበበት ስለሆነ ክርክር እንዲያቀርብበት ማድረግ ወይም ያስቀርባል ስንል በግልጽ ማጽናት ይኖርብናል።  በከፊል ስናጸና ያስቀርባል ካልነው ጭብጥ ጋር ያለውን ቁርኝት ማየት እና እንዳይጋጭ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

# የቀጠለ....

- በአፈጻጸም የታሰረ ሰው ይግባኝ ሲያቀርብ መልስ ሰጪ ሊጠራ ይገባልን ?

- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 329(1)- በይግባኝ ደረጃ አዲስ ክርክር ማቅረብ የተከለከለ ነው። በስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ፣በመቃወሚያው፣በማስረጃው ላይ ክርክር እንዲያቀርቡ ላልተፈቀደላቸው እና ዕድሉን በይግባኝ ደረጃ ለሚያገኙ ተከራካሪዎች ውጤቱ ምንድን ነው?

- መስቀለኛ ተቃውሞ የሚመራበት ስርዓት የመደበኛውን ይግባኝ አቀራረብ ይከተላል

- በመቃወሚያዎች ላይ በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ ሲቀርብ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሊወሰን ይችላልን?

# የቀጠለ....

- ክርክሩ እንደገና እንዲታይ ከተመለስ በ=ላ በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ ሲቀርብ አስቀድሞ ክርክሩ እንደገና እንዲታይ የተሰጠው ውሳኔ ሊመረመር ይችላልን?

- ክርክሩ እንደገና እንዲታይ ከተመለስ በ=ላ ክስና መልስ ሊሻሻል ይችላልን?

- የጸደቀ ዕርቅ ላይ- ለምሳሌ- ነጻ ፈቃዴን ሳልሰጥ ስምምነቱ ጸደቀብኝ ቢል- ይግባኝ ሊቀርብ ይችላልን?

- የዕግድ ክርክር ዋናው ፍሬ ጉዳይ ሳይወሰን ይግባኝ ማቅረብ ይቻላልን?

# የፍርድ አፈጻጸም

1. በውክልና ስለማስፈጸም - የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 374(1) - ዋናውን ፍርድ ከወሰነው ፍርድ ቤት  ስልጣን ጋር እኩል ነው ሲል ምን ማለት ነው?

- የጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና ሰበር ችሎት ለወረዳ ፍርድ ቤት ፍርድ እንዲያስፈጽም ውክልና ቢሰጡ ወረዳ ፍርድ ቤቱ የጠ/ፍ/ቤት ስልጣን አለው ማለት ነው?ይግባኙስ የት ነው የሚቀርበው?

- በዚህ ረገድ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ስልጣናቸው እኩል ነው በማለት መወሰኑ ህጋዊ ነውን ?

# የቀጠለ....

- መተርጎም ያለበት ውክልና የተሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ሲያስፈጽም ፍርዱን እንደፈረደው ፍርድ ቤት መስሎ፣ሆኖ ያስፈጽማል ተብሎ ሊሆን አይገባምን?

- በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 418 መሰረት ተቃውሞ ያለው ሰውስ የት ያቀርበዋል ?

- ውክልና የተሰጠው ፍርድ ቤት ሌላ ክልል የሚገኝ ቢሆን በወሰነው ውሳኔ ላይ ይግባኙ የት ይቀርባል?

- ውክልና የተሰጠው ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን ማገድ ይችላልን?

# የቀጠለ....

2. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 377 መሰረት የተወሰነበት ሰው በፍርድ ባለመብቱ ላይ ክስ ካቀረበ አፈጻጸሙን ፍርድ ቤቱ ሊያግደው ይችላል፡፡

- የትኛው ፍርድ ቤት ? የዕግድ ጥያቄው ክስ ከቀረበበት ወይስ አፈጻጸሙን ከያዘው ችሎት ነው የሚቀርበው ?

- አፈጻጸሙ የሚታገደው ሙሉ በሙሉ ወይስ አዲስ በቀረበው የክስ ሀብት መጠን ?

# የቀጠለ....

3. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.384 መሰረት የአፈጻጸም ክርክር የይርጋ ጊዜ 10 ዓመት ነው፡፡

- የቀለብ ውሳኔ በ 9 አመቱ እንዲፈጸም ቢጠየቅ በቤተሰብ ህጉ ቀለብ ከ 3 ወር በላይ ሊጠየቅ አይገባውም ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል ? የቤተሰብ ህጉ ለአፈጻጸም ክርክር ወይስ ከፍርድ በፊት መብትን ለማረጋገጥ ነው የሚፈጸመው ? ወይስ የቤተሰብ ህጉ special and latest ነው ተብሎ prevail ማድረግ አለበት ?

- የአፈጻጸም ክስ አቅርበው ንብረት በማጣት የሚዘጉ ፋይሎች የይርጋው ጊዜ ይመለከተዋልን? የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.478 ዳኝነት በነጻ የታየላቸው ሰዎች በ 10 ዓመት ውስጥ ሃበት ካላገኙ ለተገለገሉበት ክፍያ አይጠየቁም የሚለው በ analogy ሊወሰድ ይችላልን ?

# የቀጠለ....

- በአሰሪና ሰራተኛ ህግ መሰረት ወደ ስራ እንዲመለስ ውሳኔ የተሰጠው ሰራተኛ  የአፈጻጸሙን ክስ 10 ዓመት ድረስ አዘግይቶ ማቅረብ ይችላልን?

- ከተቻለ አሰሪው 10 ዓመት ሁሉ በቦታው ሌላ ሰራተኛ መቅጠር አይችልምን ?

- 10 ዓመት ድረስ ማዘግየት አይችልም ከተባለ ማቅረቢያ ጊዜው ስንት ነው ?

- የይርጋ ክርክሩን ፍርድ ቤቱ ሊያነሳው ይችላልን? የአፈጻጸሙ ደረጃ የት ላይ እያለ ? የሀራጅ ማስታወቂያ ከወጣ በ=ላ ይርጋውን ማንሳት ይቻላልን ?

# የቀጠለ....

4. በብድር ውሳኔ ለውሳኔው መሰረት የሆነው ውል መሰረት ተደርጎ በፍርድ ባለመብቱ ላይ የአራጣ ወንጀል ክስ ቢቀርብ አፈፃፀሙን ያግደዋልን ?
5. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 386(2) መሰረት የፍርድ ባለዕዳ በመሃላ ቃል ተደግፎ የማይፈጽምበትን ምክንያት፣ ንብረት ወይም ገንዘብ ያለው የሌለው መሆኑን ያስረዳል፡፡
6. ፍርድን ለመፈጸም በዋነኛነት የፍርድ ባለዕዳውን ንብረት መከተል አለብን፡፡ የፍርድ ባለዕዳው መቅረብ ግዴታ የሚሆነው ገንዘብ እንዲከፈል ከተፈረደ ነው፡፡ መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ ከቀረ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 386(4) መሰረት ታስሮ እንዲቀርብ ሊታዘዝ ይችላል፡፡ እነዲቀርብ እንጂ ፍርዱ እስኪፈጸም እንዲታሰር አይደለም፡፡

# የቀጠለ....

- የፍርድ ባለዕዳ የሚታሰረው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.387 መሰረት ለአፈጻጸሙ መሰናክል ከሆነ፣ ንብረት ካሸሸ፣ ለመሰወር ካቀደ እና በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 389 መሰረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ብቻ ፍርዱ ካልተፈጸመ ነው።
- ሊታሰር የሚችለው እስከ 6 ወር ሲሆን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 390 መሰረት ፍርዱ ከተፈጸመ ወይም ባለገንዘቡ እንዲፈታ ከጠየቀ የዕስራት ጊዜው ሳይደርስ(ሳያልቅ) መፈታት አለበት።

# የቀጠለ....

7. ፍርድ ያረፈው መሬት ላይ ከሆነ ፍርዱ እንዴት ይፈጸማል? መሬቱን ዛሬ ከፍርድ ባለዕዳው አስረክበን ነገ መልሶ ቢቀማ የአፈጻጸም ክርክሩ ሊቀጥል ይችላል ወይስ አዲስ ክስ ማቅረብ ነው ያለባቸው?

- የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ፍርዱ ተፈጸመ የሚባለው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰርቶ ሲረከቡ ነው ማለቱ ህጋዊ ነውን?

-ቢያንስ በተገቢው ሁኔታ በቁጥጥር ስር እስኪሆን እና በንብረቱ መጠቀም እስኪጀምሩ አፈጻጸሙ እንዳላለቀ መቆጠር የለበትምን?

# የቀጠለ....

- በተመሳሳይ ወደ ስራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ ፍርዱ ተፈጸመ የሚባለው መቼ ነው ወደ ስራ ዛሬ ተመልሶ ነገ ከስራ ቢሰናበት አፈጻጸሙን በመቀጠል ማስፈጸም ይችላልን?
- የተሰናበተበት ምክንያት ተጣርቶ አዲስ ምክንያት ከሆነ አዲስ ክስ ማቅረብ ወይም የተሰናበተው ፍርዱን ለመፈጸም አሰሪው እምቢተኛ በመሆኑ ብቻ መሆኑ ከተረጋገጠ አፈጻጸሙን በመቀጠል ፍርዱን ማስፈጸም ምክንያታዊ ይሆናል።

# የቀጠለ....

8. በአፈጻጸም ስለሚሸጥ ንብረት

- የገጠር ቤት ሊሸጥ ይችላልን ወይስ ቤቱ ፈርሶ ፍርስራሹ ነው የሚሸጠው? ቤቱ ከተሸጠ የÒሮ መሬቱ ዕጣ ፈንታ ምን ይሆናል ? የኢ.ፌዲ.ሪ ህገ-መንግስት የገጠር ቤት እንዳይሸጥ ይከለክላልን ? ቤቱ ከፈረሰ የሚጎዳው የፍርድ ባለዕዳው ነው የንብረቱ ዋጋ በጣም ይቀንስበታል።

- የዕርሻ መሬትን ፍርድ ለማስፈጸሚያ ማከራየት ይቻላልን? መሬትን በዕዳ መያዝ ይሆናል ውጤቱ?

- የከተማ ሰነድ-አልባ ቤት በአፈጻጸም ሊሸጥ ይችላልን? ከተሸጠ ገዥው በቤቱ ላይ ያለው መብት የት ድረስ ነው? ማዘጋጃ ቤት ቤቱን እንዲገምት ሲታዘዝ አልገምትም ይላል ማስገደድ ይቻላልን?

# የቀጠለ....

9. ከፍርድ ቤት ውጭ ፍርድን ስለመፈጸም - የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 396(4) - በፍርድ ቤት ያልተመዘገበ ክፍያ በማናቸውም ፍርድ አስፈጻሚ ፍርድ ቤት ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህ ማለት ፍርድ ከፍርድ ቤት ውጭ እንዲፈጸም ስነ ስርዓት ህጉ ፍላጎት የለውም ማለት ነው?
10. በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 428(2) መሰረት በሁለተኛ ሀራጅ ያልተሸጠ ንብረት የፍርድ ባለመብቱ እንዲረከበው ይደረጋል፡፡ በልዩነት የመጣ ገንዘብ ካለ ለፍርድ ባለዕዳው መመለስ ይኖርበታል

# የቀጠለ....

- የፍርድ ባለመብቱ ልዩነቱን ገንዘብ ለመክፈል ከተረከበው ንብረት ውጭ ሌላ ንብረት ባይኖረው የተረከበው ንብረት ሊሸጥ ይችላል ?
- ከተሸጠ 3ኛ ሀራጅ አይሆንም ? ተጫራች ቢጠፋ መልሶ ንብረቱን ለባለዕዳው ሊያስረክብ ነው ? 3ኛ ሀራጅ ካልተፈቀደ የልዩነቱ ገንዘብ መቼና እንዴት ይመለሳል ?

11. የባልና ሚስት ወይም ውርስ ንብረት በዓይነት ለመክፈል አፈጻጸሙ እንዴት ይመራል ? ሳይበላሽ የሚከፈል ከሆነ ነገር ግን ሲከፈል የማዘጋጃ ቤት መመሪያ ከሚያዘው የቦታ መጠን በታች ከሆነ ንብረቱ በዓይነት ሊከፈል ይችላልን?

# የቀጠለ....

12. በአንድ ጉዳይ በተለያየ ተከራካሪ ሁለት የይግባኝ መዝገብ ተከፍቶ የሚጋጭ ውሳኔ ቢሰጥ እንዴት ይፈጸማል ?

- ፍርዱና ውሳኔው ቢጋጭ፣ የገጠር መሬት ላይ የመሬቱ አዋሳኝ እና የመሬቱ መጠን መካከል ልዩነት ቢኖር እንዴት ይፈጸማል ?

13. የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 418 እና 419 መሰረት ለፍርድ ማስፈጸሚያ በተያዘው ንብረት (ፍርድ ያላረፈበት ንብረት) ላይ መብት አለን የሚሉ ወገኖች መቃወሚያ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 418(3) መብቱ የሚረጋገጠው በጽሁፍ ማስረጃ ነው ይላል. The English version says “evidence”.

# የቀጠለ....

- በሰነድ ሊረጋገጡ የማይችሉ ንብረቶችስ?
  - መብት አለን የሚሉ ወገኖች አዲስ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡

14. በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ስለሚፈጸምበት ሁኔታ(የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.456 እና ተከታዮቹ)

  - የአፈፃፀም ክሱ በኢትዮጵያ በየትኛው ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላልን ? ንብረቱ በሚገኝበት ክልል ሆኖ ግን በየትኛው ዕርከን ፍርድ ቤት ይቀርባል ?
  - ፍርዱን የፈረደው ፍርድ ቤት የሚገኝበት ሀገር በኢትዮጵያ የተሰጠውን ፍርድም የሚፈጽም መሆኑ ሲረጋገጥ
  - የፍርድ ባለዕዳው የመደመጥ መብቱ መከበሩ ሲረጋገጥ
  - ፍርዱ ለህዝብ ሞራልና ጸጥታ ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ

# የፍርድ አፃፃፍ

- የፍርድ አፃፃፍ የሚጀምረው ጉዳዩን በደንብ ከመረዳት እና ከ brief ስርዓት ነው። brief መደረግ ያለበት ምን መወሰን እንዳለበት ብቻ ሳይሆን ትንታኔው እና ምክንያቱም ጭምር ነው
- በተግባር የሀሳብ ድግግሞሽ፣ በጣም የረዘመ ወይም ያጠረ፣ የሀሳብ ፍሰት የሌለው፣ መደበኛ ያልሆኑ ቃላትን አለመጠቀም
- የተጠየቀውን ዳኝነት በሙሉ ዕልባት መስጠት- በአንድ ጉዳይ የሰሩትን ቤት ግምት እንዲከፈላቸው ተወሰነ። በአፈጻጸም ክርክር የሰሩት ቤት የለም በሚል ግምት ለማስከፈል ባለመቻሉ ጉዳዩ ሁለት ጊዜ በክልሉ ሰበር ችሎት ታይ~ል። ሌላ ቆየት ባለጉዳይ ፍርድ ቤቱ የቦታ ክርክር ላይ ቀበሌው ለከቶ ያካፍላቸው በማለት መዝገቡን ዘግ~ል። በሁለቱም መዝገቦች የፍርድ አፃፃፍ ጉድለት ያለባቸውና ፍርዱን ለአፈፃፀም ችሎቱ እና ለቀበሌ አስተዳደር የሰጡ ናቸው።
- የቀረቡ ክርክሮችንና ማስረጃን በሙሉ መመልከት
- ትንታኔ፣ምክንያት፣የህግ ትርጉም መስጠት

# ወጭና ኪሳራ

- ዓላማው - ፍትሃዊነት ለማምጣት እና ተገቢ ያልሆነ ክርክር እንዳይቀርብ ለማድረግ
- የወጭና ኪሳራ ዝርዝር ማመልከቻ ማቅረብ የዳኝነት ክፍያ አያስፈልገውም
- ለመወሰን- የጉዳዩ ዓይነት፣ የወሰደው ጊዜ፣ የተከራካሪዎች አድራሻና ፍርድ ቤቱ የሚያስችልበት ቦታ ርቀት፣ ከተጠየቁት ዳኝነቶች አንጻር የተወሰነውን ማመዛዘን- ለምሳሌ-1 ሚሊዮን ጠይቆ 100ሺ ቢወሰን በ 1 ሚሊዮን የክስ ገንዘብ ኪሳራ ሊከፈል አይችልም
- መንግስት የዳኝነት ክፍያ አይከፍልም ቢረታ ተረቺው የዳኝነት ሊከፍል ይችላልን?

# የቀጠለ....

- ወጭዎች- የዳኝነት ክፍያ፣ የመጥሪያ፣ ለማስረጃና ለተራነሰፖርት፣ ለምስክር አበል፣ የጠበቃ አበል፣ የማመልከቻ ማፃፊያ
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 463(3)-ኪሳራ በግምት ወይም በቁርጥ ሊከፈል እንደሚችል ይገልጻል፡፤ የሚመከረው ግን በተለይ Trial ችሎት ላይ የወጭና ኪሳራ ዝርዝር ቀርቦ ክርክር ተደርጎበት እንዲወሰን ነው
- በድህ ደንብ ያቀረበ ሰው ከረታ በረታው ልክ በአፈጻጸም ክርክሩ ላይ የዳኝነት መክፈል አለበት(የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.476)

# የቀጠለ....

- ባልረታበት የክስ መጠን ደግሞ በኑሮው ሀብት በ 10 ዓመት ውስጥ ካገኘ አገልግሎቱን ላገኘበት ክፍያውን የመክፈል ግዴታ አለበት
- የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 465- ሆነብሎ ሀሰተኛ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበ ተከራካሪ ለእያንዳንዱ ሀሰተኛ ክርክር ከ 500 ብር ያልበለጠ ገንዘብ  በካሳ መልክ ይከፍላል።

አመሰግናለሁ።